የአወሊያ ጤና ተቋማት ፡-

የአወሊያ ጤና ጣቢያ አዲስ አበባ በየካቲት/1985 የአወሊያን ህጻናት ማሳደጊያ መቋቋምን ተከትሎ ለህጻናቱ አገልገሎት እንዲሰጥ ታስቦ በክሊኒክ ደረጃ ተጀምሮ ወደ ጤና ጣቢያ በማሳደግ ለአካባቢው ህብረተሰብ የተሟላ የጤና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ተቋም ነው።ጤና ጣቢያው የመከላከል፤ የማዳን፤ የላብራቶሪ፤ የራጅ፤የአልትራሳውንድና የመድሃኒት አገልግሎት በተጠናከረ ሁኔታ ይሰጥ ነበር። እስከ 2002 ድረስ በአማካኝ 414 እናቶች የቅድመ ወሊድ ተጠቃሚ፤107 እናቶችና ህጻናት የክትባት አገልግሎት፤ 20 እናቶች የወሊድ አገልግሎት፤ 23 ታካሚዎች የሳምባነቀርሳ ክትትል አገልግሎት፤ 23 ግለሰቦች የኤች.አይ.ቪ ምርመራና የምክር አገልግሎት፤180የጥርስ ታካሚዎችን፤ 1033 ላቭራቶሪ ተጠቃሚዎችን፤ 1000 የሚሆኑትን የመድሃኒት አገልግሎት፤ 900 ታካሚዎች በተመላላሽነት አገልግሎት ሰጥቷል።


አወሊያ ጤና ጣቢያ

የሚገርመው ግን ከ2003 መጅሊሱ ከተረከበው በኋላ ፈቃድ እንኳ ለማደስ ተቸግሮ ሥራው ተዳክሞ እንዳይሞት እንዳይድን ሠራተኛ ብቻ አየገባ እንዲሁ የቆዩ ሲሆን ፍቃዱ በ2010 ከሰባት ዓመት በኋላ የታደሰ ቢሆንም አሁንም በቀን ከአስር እና ከአስራ አምስት ታካሚ በላይ እያስተናገደ አይደለም።

በ2012 አንድ ዶክተር ሜዲካል ዳይሬክተር የተቀጠረ ሲሆን በአወሊያ የቀድሞ ተማሪዎች በብር 264,000 ብር ሲቪሲ ማሽን በመግዛታቸው በተወሰነ ደረጃ መነቃቃት ጀምሯል። በጤና ጣቢያው 17 የህክምና ባለሙያዎችና 15 የድጋፍ ሰጪ በድምሩ 32 ሰራተኞች ይገኛሉ።

በአሁኑ ወቅት በጤና ጣቢያው ያለውን የገንዘብ ገቢና ወጪውን በተመለከተም ወርሃዊ የሚሰበሰብ ብር 27,087 ሲሆን በወር ወጪ የሚደረግለት ለደመወዝ ብር 155,143 ለስራ ማስኬጃ ደግሞ ብር 17,362 ራሱን ለመቻል ብር 145,418 ገቢ ማስገኘት ይጠበቅበታል።

ለሆስፒታል አገልግሎት እንዲውል ታስቦ በሸህ አብደረህማን መባረክ ግንባታው ሳይጠናቀቅ ከአሰራ አምስት ዓመት በላይ እንዲሁ እንደቆመ የሚገኘው የአወሊያ ሆስፒታል ህንጻ አንዱ አሳዛኝ ጉዳይ ነው። ሸሁ ይህንን ታላቅ ሥራ እንዳያጠነቅቁ ተወንጅለው ከሀገር ወጡ። ሌላውም አስተባብሮ እንዳያሠራው እንቅፋት በዛበትና ድፍን 15 ዓመታት ይህን የመሰለ ሕንጻ ታቅፎ መቀመጥ አንገት የሚያስደፋ አሳፋሪ ተግባር ነው።



ለ15 ዓመታት ሳይጠናቀቅ የቆመው
የአወሊያ ሆስፒታል ሕንጻ

ከዕለታት አንድ ቀን ረመዳን /1441 ግንቦት /2012 አንድ የጽሁፍ መልዕክት በዋትሳፕ ደረሰኝ። ከቱርክ እጨ ዶክተር አሊ ሁሴን ነበር የተላከው። ሰላምታ ካቀረበልኝ በኋላ አስታውሼው እንደሆን ጠየቀኝ። በርግጥ ልረሳው የምችል አልነበረም። በአንድ የወላጆች ስብሰባ ወቅት መልዕክት አስተላልፎ መውጣቱ ትዝ ይለኛል። ስብሰባው በመምህራን የደመወዝ ጭማሪ ዙሪያ የነበረና በእለቱ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ሊቀመንበር እና የአወሊያ የበላይ የነበሩት ሙፍቲ ሐጂ ዑመር ኢድሪስ ተጠርተው መቅረታቸው እንዲሁም ጭማሪውን ከፈለገ መጅሊስ ይጨምር ካልቻለ አወሊያን ያስረክበን የሚሉ ነውጠኛ ሀሳቦች ይነጸባረቁ የነበረበት ስብሰባ ነበር። በወቅቱ ዶክተር አሊ የሚያረጋጋ መልዕክት አስተላልፎ መወጣቱን አስታወስኩ። እናም ከዚያ በኋላ ስሜቱ በጣም እንደተነካና በውጪ የሚኖሩ ወንድምና እህቶችን በማስተባበር ቢያንስ የሆስፒታል ህንጻውን ለማስጨረስ እንዳሰቡ ገለጸልኝ።

በቀን /2012 እሱ ከቱርክ፤ ከቨርጀኒያ ፈትሁዲን ኢብራሂም፣ ከጀርመን ደግሞ አቶ ሙሀመድ ሀሰን ለመገናኘትን እኔም ስለሆስፒታሉ አጭር መግለጫ እንዳዘጋጅና ማብራሪያ እንዳቀርብ ተስመምተን ተለያየን። በተባለው ቀንና ሰዓት ሶስታችን ከ11፡30- 1፡00 ሰዓት ሰፊ ውይይት በZOOM MEETING አደረግን። በቀጣይ ይህንኑ ገለጻ ሰፋ በማድረግ ለሌሎች ተሳታፊዎች ጨምሮ ለማቅረብ ተስማማን። ከቦርዱም እነ ዶ/ር ጀማል ሙሀመድ እና ሌሎች እንዲሳተፉ ተደረገ። በወቅቱ ከ40 በላይ ተሳታፊዎች ውይይቱ ላይ ታደሙ። በዚሁ ለሆስፒታሉ ህንጻ የማሰሪያ የገንዘብ ማሰባሰብ ተጀመረ። በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አወሊያ ጤና ጣቢያ አካውንት ቁጥር 1000006580335 ውስጥ ገቢ እንዲያደርጉ ከፍተኛ የማስታወቂያ ስራ ተሰራ። ከደቡብ አፍሪካ ጀመሳ ብቻ 1.7 ሚሊዮን መሰብሰቡ ተገለጸ። ሌሎች በተናጠል ማስገባት ጀምረዋል። በእቅዳችንም ለግንባታው እስከ 6 ሚሊዮን ብር፤ ለማስፋፊያ፣ 2.5 ሚሊዮን ለጤና ጣቢያው መሳሪያዎች ግዥ 1.5። በድምሩ እስከ 10 ሚሊዮን ብር እንደሚያስፈልገን በይፋ ገለጽን። እንቅስቃሴው ተጠናክሮ ቀጥሏል። ገንዘቡ እስከ ግንቦት 30/2012 ገቢ ከተደረገልን በ90 የስራ ቀናት በማጠናቀቅን ጥቅምት መጨረሻ ለማስመረቅ መታቀዱን ይፋ አደረግን።

<u>የአልከሶ ፖሊ ክሊኒክ</u>

የአልከሶ ፖሊ ክሊኒክ ደቡብ ስልጤ ዞን አልከሶ ቀበሌ የካቲት 1985 ተመሰረተ። በአካባቢው ምንም አይነት የጤና ተቋም ባልነበረበት ወቅት የስድስት ቀበሌ ገበሬ ማህበር ማህበረሰብ ወደ ቡታጅራ ሆስፒታል 30 ኪሎ ሜትር መጓዝ ግድ ነበር። ፖሊ ክሊኒኩ የመከላከል፤ የማከምና ሌሎች ተዛማጅ ስራዎች ማለትም የላብራቶሪና በተደራጀ መልኩ ከውጪ በሚመጡ ምርጥ ምርጥ መድሃኒቶች አገልግሎት ይሰጥ ነበር። በወቅቱ በዚያ የገጠር ቀበሌ ዶክተር የነበረበት ብቸኛ ክሊኒክ ነበር።

ከሰኔ/2003 ጠቅላይ ም/ቤቱ ከተረከበው ጊዜ በኋላ የወረዳው ጤና ጽ/ቤት ተገቢውን አገልግሎት መስጠት አልቻለም በማለት ተጨማሪ ህንጻ በመገንባትና ባለሙያዎችን በራሱ በመቅጠር፤ መድሃኒት በማቅረብና ገቢውንም በራሱ በመሰብሰብ ላይ የሚገኝ ሲሆን ጠቅላይ ምክር ቤቱ የባለቤትነት ስሙንና የዘጠኝ ባለሙያዎችን ደሞዝ በመክፈል ይዞታውን አስከበረ። በእውነቱ ይህ ብቻ በቂ አይደለም። በዚህ ሁኔታ ልዩ ትኩረት ካልተሰጠው መንግስት ሊያጠቃልለው እንደሚፈልግ ግልጽ ነው።



በአሁኑ ወቅት በክሊኒኩ 6 ባለሙያና 3 የድጋፍ ሰጪ በድምሩ 9 ሰራተኞች አሉ። በክሊኒኩ ያለውን ገቢና ወጪ ብንመለከት፡- ወርሃዊ የሚሰበሰብ ምንም ገንዘብ የለም። ወርሃዊ ወጪ የሚደረግ ለደመወዝ ብር 21.344 ራሱን ለመቻል ብር 21344 ገቢ ማስገኘት ይጠበቅበታል፡፤

<u>የሀረር አብደል ክሊኒክ</u>

በሀረሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሀረር ከተማ የሚገኘው ሀረር አብደል ክሊኒክ በ1985 እንደተመሰረተ ቢገለጽም አገልግሎት የጀመረው ግን በ1992 በኢንተርናሽናል ኢስላሚክ ሪሊፍ ኦርጋናይዜሽን አማካኝነት ነበር። ክሊኒኩ ያለበት ቦታ አባድር ት/ቤት ውስጥ ሲሆን ያለበትን ህንጻ ሀጅ ቱሬ እንደሰሩት ይነገራል። ክሊኒኩ በጥርስ ህክምና አገልግሎት ከፍተኛ እውቅና ነበረው። በአሁኑ ወቅት አገልግሎቱ እጅግ ተዳክሞ ይገኛል።





በክሊኒኩ ያለው የሰው ኃይል 10 ሰዎች ሲሆኑ 4 ባለሙያዎች 6 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ናቸው። በአሁኑ ወቅት ያለው የገንዘብ ገቢና ወጪውን በተመለከተም ወርሃዊ የሚሰበሰብ ብር 870 ሲሆን ወጪ የሚደረግ ለደመወዝ ብር 25,674 ለስራ ማስኬጃ ደግሞ ብር 109 ራሱን ለመቻል ብር 24,913 ገቢ ማስገኘት ይጠበቅበታል።

የወሊሶ መለስተኛ ክሊኒክ፡-

ከጥቅምት 2001 ጀምሮ በወር በአማካይ ከ150 በላይ ለሚሆን የአካባቢው ህብረተሰብ እና በግቢው ውስጥ ለሚገኙት ሕጻናትና ሠራተኞች የጤና አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ ሲሆን ከሰኔ 2003 መጂሊሱ ከተረከበው በኋላ ግን አገልግሎቱ እየተዳከመ በመሄድ አሁን አንድ ባለሙያ ብቻ እንዳይዘጋ እየጠበቀ ይገኛል።

የእርዳታና ልማት ዘርፍ

የአወሊያ ህጻናት ማሳደጊያ ማዕከል

የአወሊያ ህጻናት ማሳደጊያ በአለም አቀፉ ኢስላማዊ እርዳታ ድርጀት ከቀድሞው ሠራተኛና ማህበራዊ ሚኒስቴር ስር በነበረው የህጻናትና ወጣቶች ኮሚሽን ጋር በተደረገ የፕሮጀክት ስምምነት ታህሳስ 1984 ስራውን ጀመረ። 1977 በሀገራችን በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ 80 ህጻናት በመቀበል ሰራውን የጀመረው ማዕከሉ በሂደት ቁጥራቸውን ወደ 200 በማሳደግ ሙሉ አገልግሎት በመስጠት ብዙዎችን ኣሳድጎና አስተምሮ ለፍሬ ያበቃ ተቋም ሲሆን በሰኔ 2003 መጀሊሱ አወሊያን እንደተረከበ ከፈጸመው ክፉ ተግባር በማሳደጊያው ውስጥ የነበሩ ህጻናትን ከግቢ ወጥተው እንደዲበተኑ ማድረጉ ነበር። ከዚያ ጀምሮ አገልግሎቱ ተቋርጧል።



የብረታብረትና የእንጨት ሥራ ወርክሾፕ

በ1996 ነበር የትምህርት ቤቶችን ወንበር፤ ጠረጴዛ፤ ሰሌዳና የተለያዩ የእንጨትና የብረታብረት ስራዎች በዘመናዊ ሁኔታ የሚሰራበት የስራ ክፍል ሲሆን በውስን ባለሙያዎች አስገራሚ ስራ የሚሰራበት ቦታ ነው።





አወሊያ ነጻ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት

በአዲስ አበባ በአወሊያ ዋናው ግቢ በ1996 በሸህ አብዱረህማን የተቆፈረው የከርሰ ምድር ውሃ ጥልቀቱ 117 ሜትር ሲሆን ከአስራ ሰባት አመት በላይ ያለምንም ክፍያ ለአካባቢው ህብረተሰብ ንጽህ የመጠጥ ውሃ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። ይህ የከርሰ ምድር ውሃ ለመጀመሪያ ጊዜ ብልሽት ገጥሞት አገልግሎት ያቆመው በግንቦት 2011 ዓ.ል ላይ ሲሆን የመስጅድ ጀማዎችን በማስተባበር ከዘጠና ሽብር በላይ ተዋጥቶ እንደገና ተጠርጎ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል። 2012 ተጨማሪ ባለ 20000 ሊትር ሮቶ በመግዛትና የውሃ ቧንቧዎችን በውጪ እንዲጨመር ወድ 5000 ሪያል በሳዑዲ ኤምባሲ በኩል በተደረገ ድጋፍ የማሰፋፊያ ሥራ ተሠርቷል።







ለ17 አመት ያለማቋረጥ ለአካባቢው ማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለየክርሰ ምድር ውሃ

<u>የአስክሬን እጥበትና የቀብር ሥርዓት ማስፈጸሚያ</u>

በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን ቀብር ማስፈጸሚያ ወጪ ተከትሎ በየቦታው የሚታየውን አስክሬን አስቀምጦ መለመን የሚኖረውን አሉታዊ የአገር ገጽታ መሰረት በማድረግ እና የተመቻቸ አስክሬን ማጠቢያና መገነዣ ቦታ አለመኖር ለዚህ ፕሮጀክት መመስረት ምክንያቶች ነበሩ። ፕሮጀክቱ በየካቲት 1997 የተመሰረተ ሲሆን በዋናነት የሚሰጠው አገልግሎት በሚደርስ የስልክ ጥሪ አስክሬን ካለበት ቦታ እስከ ድርጅታችን ድረስ ከዚያም ታጥቦና ተገንዞ የቀብር ስነ ስርዓት የሚፈጸምበት የቀብር ቦታ ድረስ በነጻ የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል። ሽሪአው በሚፈቅደው መሰርት የወንድና የሴት ክፍሎች ውስጥ የእጥበት አገልግሎት መስጠትና የገንዘብ አቅም የሌላቸው የቀብር ክፍያ ሁሉ ተሸፍኖላቸው የቀብር አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል። በአማካኝ በየወሩ 60 አስከሬኖች ቀብር ይፈጽማሉ።

2007 ከተፈጸሙ ወሳኝ ተግባራት አንዱ የነበረችውን አሮጌ ፒካፕ የአስከሬን ማመላለሻ መኪና ሠራተኛውን በማስተባበርና የተወሰኑ ባለሀብቶችን ድጋፍ በመጠየቅ ዘመናዊ፤ ጠንካራና በአንዴ ሁለት አስክሬን መያዝ የሚችል ሸፍን ዶልፊን መኪን በመግዛት በአሁኑ ወቅት አስክሬን በጸሐይና በዝናብ ከመንገላታት ድኗል። በአወሊያ የአስከሬን እጥበት ሲነሳ በዋናነት የኡስታዝ ናስር አሊ ጥረት እንዲሁም ከሴቶች አይሻ ሙሀመድን ልፋትና ድካም መቸም አይዘነጋም።



የአስክሬን እጥበት ክፍል



ለበርካታ ዓመታት ጀናዛ

እለቱ ረቡዕ ቀኑ /2006 የሚጀመንት ስብሰባ የመጀመሪያው አጀንዳችን ነበር። ከራሳችን ጀምረን ሠራተኛን በማሰተባበር ብዙ ሥራ መስራት የምንችል፣ ተረጅ ብቻ ሳይሆን መርዳት የምንችል መሆናችንን የምናሳይበት አጀንዳ ነበር። በመሆኑም ለዘመናት በፒካፕ መኪና በጸሐይና በዝናብ ለሚንገላታው አስክሬን አንድ ሽፍን ጠናካራ መኪና መግዛት አለብን በማለት መነሻ ሀሳቡን አቀረብን። በሚጀመንት አባላት በደስታ በሙሉ ድምጽ ተቀበለው እዚያው መድረክ ከ500ብር እስከ 5000ብር ቃል ተገባ። ሀሳቡ ወደታች እንዲወርድ በማድረግ ሠራተኛው በደስታ እስከ 120.000 ብር ያውዋጣ ሲሆን ሌሎች ተባባሪዎች ተጨምረውበት 660.000ብር ያወጣ ጠንካራ፤አዲስ በአንዴ ሁለት ጀናዛ የሚይዝ መኪና መግዛት ተችሏል። በዚህ ሂደት የወንድማችን ሙስጦፋ አብዳላ የማስተባበር ጥረት የማይዘነጋ ነበር። ከዚህ የተረዳሁት ቢኖር የአወሊያ መምህራን እና ሰራተኞች የሚያስተባበራቸው ማጣት እንጅ ታሪክ መስራት የሚችል ሃይል መሆኑን ነው።



በመምህራንና ሰራተኞች የተገዛው አዲሱ የአስክሬን ማመላላሻ መኪና

ሰመራ ፕሮጀክት

ለማህበራዊ አገልግሎት የሚውል 46338 ስ.ካ.ሜ ባዶ ቦታ በአፋር ክልል ሰማራ ከተማ በዓለም አቀፉ እርዳታ ድርጅት ስም የነበረ ሲሆን ይህ ሰፊ ቦታ ምንም ሳይሰራበት ከአስር ዓመት በላይ ስለቆይ መንግስት ወደ መሬት ባንክ ሊወስደው እንደሆነ ስንሰማ ወደቦታው በመሄድ ስሙን በማዞር ካርታው በአወሊያ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እንዲሆን በማድረግ በጊዜው ከመቀማት አድነነዋል። ነገር ግን መጂሊሱ ለአጥር ማሳጠሪያ እንኳ በጀት ለመስጠት ፍቃደኛ ባለመሆኑ መንግስት ሊወስደው ሲል የአፋር ክልል እስልምና ጉዳይ ም/ቤት በስሙ ካርታውን ማዞሩን በደብዳቤ ለጠቅላይ ም/ቤቱ



